"***ፍጹም ነው እምነቴ***" ጸሀፊ አቶ ነሲቡ ስብሀት

ሰለሞን ከተማ ቦሩ፣ ታዛቢ

<u>"***ፍጹም ነው እምነቴ***" ይናገራል</u>

ይህን የአቶ ነሲቡ ስብሐት መጽሐፍ ሳነብ፣ ወደሁዋላ ሄጄ ብዙ ነገር እንዳሰላስልና እንዳይ ብቻ ሳይሆን ገፈቱንና ህመሙን፣ ጭንቀቱንና ብሶቱን፣ የተሸናፊነት መሪር ቁጭቱን እንድነከርበት አድርጎኛል። ያለፉትን፣ የወደቁትን፣ የቆሰሉትን፣ የጨለመባቸውን፣ ተስፋቸው የተቆረጠውን፣ በተሰናከለ ህይወት ውስጥ የሚጉዋዙትን የዛን ዘመን ጀግና ወጣቶች ሁሉ በሚንከራተት አይነ ህሊናዬ እንድዳሥሳቸው፣ እንድባባላቸው አድርጎኛል። ካቻምና አንድ ልጆቻቸው በቀይ ሽብር የተገደሉባቸው አዛውንት "ኢህአፓ ይመጣል፣ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል ይህ ባይሆን" እያሉ በምሬት ሲነግሩኝ፤ በህብረተሰባችን ውስጥ የተተከለውን ቁስል እና የነፃነት ተስፋ ከዚህ መጽሀፍ ጋር እንዳቆራኘው አድርጎኛል።

ከኛ ትውልድ በፊት የነበረው የአባቶቻችን ትውልድ በኢጣሊያን ወረራ ጊዜ የነበረውን መከራና ዋይታ አስደምጦኛል። እናትና አባቴ በጣልያን ጊዜ የነበረውን ግፍና በደል በልጅነታቸው ያደረጉትን ትግልና መስዋዕትነት እያወጉን ነው ያደግሁት። እናቴ አሁን 91 ዓመትዋ ነው። አሁንም የጣልያንን ነገር ታነሳለች። ያንገሽግሻታል። በማይጨው ውጊያ ላይ ቆስሎ በወሳንሳ ወደ ቀየው በጀግንነት የተመለሰውንና መንቀሳቀስ የማይችለውን አባትዋን በተኛበት አልጋ ላይ በአካፋና በዶማ እፊትዋ ነው ጭንቅላቱን የቆፈሩት። ከዛም በድኑን በጥይት ጨረሱት፣ ቤቱንም በበድኑ ሰይ አነደዱት፣ ባንዳዎቹ።

እሷም እስረኛ ሆና የጣልያን ካምፕ ታሰረች። ካምፑ ውስጥ የተሰራው ግፍና በደል አሰቃቂነት የከፍተኛ 15ቱን ይመስላል። ደም በደም ነበር። ትንሽ ለየት የሚያደርገው በጣልያን ጊዜ የአርበኛ አንገት ተቆርጦ እስረኛው ፊት በአጣና ላይ መተከሉ ብቻ ነው፣ የአጎትዋም ጭንቅላት አንደኛው ነበር። በተጨማሪም እነዛው የአበሻ ምርኮኞች ውሃ በመከልከላቸው ምክንያት ሽንት ይጠጡ ነበር። በረሀብ በጥማት በበሽታ እዛው ካምፕ ውስጥ ይሞቱ ነበር፣ እንደ ከፍተኛ 15ቱ። የከፍተኛ 15 ደግሞ በተጨማሪ ከጣልያኑ ለየት የሚለው በማሰቃያ ዘዴዎቹ አበዛዝና መጠን የለሽ አጨካከን ሂደት ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ በአንድ ሀገር ሕግ በሚተዳደሩ፣ በአንድ ዜግነት በሚታወቁ ወገኖች መሃከል፤ ባንድ በኩል ሕግና ስርዓት በማይገዛቸው ሰብዓዊ ሕሊናቸውን በሳቱ፣ የመግደል መብት ያለገደብ የተሰጣቸው ግለሰቦች ተሰልፈው፣ በእብሪተኝነታቸው በክቡርነት በሚታወቅ ሰብዓዊ ፍጡር ገላ ላይ በደም ሲነከሩ ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ የነበረውን መንግስት የሚቃወሙና ሙሉ በሙሉ ያለህግ ሂደትና ፍርድ ሰብእናቸውን፣ ዜግነታቸውን፣ ሕጋዊ መብታቸውን በተፈጠሩበት አገራቸው ላይ ተገፈው፣ የሰብዓዊ ፍጡር ህሊና ሊቀበለዉ ከሚችለው በላይ የመከራና የጣር እስር ቤት ውስጥ ታምቀው፣ በሰው ልጅ ቄራ ውስጥ ባለተራ ሆነው ይታያሉ።

የጣልያን ጊዜ ባንዶች ለውጭ መንግስት አድረው ሕዝባቸውን ሲጨፈጭፉ የነበሩ ሲሆኑ፣ ዝርዝር የባንዳነት ምክንያታቸውና አመጣጣቸው የተለያየና የሚያስገርምም ነበር። ያም ቢሆን ከዛን ጊዜ ባንዳዎች ውስጥ እንኳዋ የሚሰሩት ግፍና በደል ከብዶዋቸውና ፀጽቷቸውም ጣልያንን የከዱም፣ መልሰው የወጉም ነበሩባቸው። እነዚህኛዎቹ የከፍተኛ 15 ባንዳዎች ውስጥ ግን ምንም ዓይነት ፀጸት አልታየባቸውም። የአገሩን ሕዝብ ጥቅም፣ ልማድና ፀንቶ የኖረ ሕግና ባህልን ከድቶ፣ የሀገሩን ሰው የሚጎዳም ሆነ የሚያስጎዳ ሁሉ ባንዳ ነው።

ከሁሉ ከሁሉ የዚህኛው ወጣት ትውልድ ታሪክ የሚያሳዝነው ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የሚባለው ግብረ-ባዕዳን አዲጋ የተመዘዘው የባዕዳን ርዕዮተ አምልኮ ተከታይ በነበሩ ምሁራን ሲሆን፣ የደም መፋሰሱን ሂደት ለማቆም ያደረጉት ጥረት አለመኖሩና፣ የመኢሶን-ደርግ ምሁራንም ወንጀለኝነታቸውን አለመገንዘባቸውና አለማቀባቸው ሲያሳዝን፤ የኢሕአፓ መሪዎችም በወቅቱ የመጣባቸውን ሀይል ተገንዝበውና አመዛዝነው አለማፈግፈጋቸውና የወጣቶችን ሕይወት በግድ የለሽነት እንዳስመተሩት ይህ የአቶ ነሲቡ መጽሀፍ ያረጋግጣል። ይህ ሁሉ ስልጣንን የተመረኮዘ ጭካኔና የተሸናፊው ድርጅት መሪዎች ግድ የለሽነት እንዴት ሊፈጠርና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቦታ ሊኖረው ቻለ ብሎ ለሚጠይቅ ሕሊና ይህ የአቶ ነሲቡ መጽሀፍ በቅጡ ይፈትናል፣ ይፈታተናል።

ድሮውንም በጣም ይገርመኝ የነበረ ነገርና ረስቸው የነበረ ጉዳይ እንደገና ትዝ እንዲለኝ "***ፍጹም ነው እምነቴ***" ከደነገዘኩበት አባነነኝ። መኢሶን ኢሕአፓ በመባባል የተለያዩት ሁለት ኢትዮጵያውያን ወገኖች፣ ለስልጣን ፍለጋም ይሁን ለሀገራችን ቀና

መንገድ በማሰብ በአንድ ላይ ሊሄዱ ወይም ሊረዳዱ ያልቻሉበት ምክንያት ምን ነበር? መኢሶን ስልጣን ላይ ካለው በአስተሳሰብም፣ በምግባሩም፣ በስነልቦናውም ከማይመስለውና ከማይመጥነው ወታደራዊ መንግስት ጋር መስማማት ሲችል፣ በብዙ መንገድ አብረው ሊራመዱ ከሚችሉ በተግባራቸውም በባህሪያቸውም እነሱን ከሚመስሉ ኢሕአፓዎች ጋርስ እንዴት መመካከርና የአጭርና የረዥም ጊዜ ልዩነትና አንድነት መፍጠር አቃታቸው? ኢሕአፓስ ቢሆን ከመርዘኛው የኢትዮጵያ ጠላት፣ በአቅዋም በአምሳልም በዓላማም ከማይመስላቸውና ከማይመጥናቸው፣ ከማይጣመዳቸው ከሻቢያና ከጀብሃ ጋር ወዳጅነት ሲፈጥር፣ እንዴት ከአምሳላቸው፣ ከአቻቸው ከመኢሶን ጋር መስማማት አልቻሉም ነበር? መኢሶን ለታክቲክ ከደርግ ጋር ወገነ፣ ኢሕአፓም ለታክቲክ ከሻቢያ ጋር ወገነ ተባለ፣ ታድያ እንዴት ይህንን አሽቀንጥረው የሚጥሉትን ጊዜያዊ ታክቲክ የተቀበለው ጭንቅላታቸው፣ በአጭርና በረዥም ጊዜ ጉዳይ ውስጥ ቆመንለታል የሚሉት አገርና ሕዝብ ሲደመሰስ፣ በወርበላው ደርግ ሲታመስ፣ የሀገርና የሕዝብ ጥፋት ሲያስከትልስ በመስማማት ፈንታ እንዴት ዝም ብለው የጥፋቱ ተቋዋራሽ ሆኑ? የሚለው ጥያቄ "***ፍጹም ነው እምነቴ***"ን የሚያነብ ኢትዮጵያዊ ልቦና ውስጥ ይቀሰቀሳል። በሁለቱ ምሁር ወገኖች መካከል የአገርና የህዝብ ጉዳት አልታሰቤነትን ምክንያት ወጣቱ ሲያንሰራራ እንመለስበት ይሆናል።

ይህ መጽሀፍ "***ፍጹም ነው እምነቴ***" በዛን ወቅት ታናናሽ ወንድሞቻችን እህቶቻችን ያለፉበትን የመረረ ሕይወት እንድናይ አድርጐኛል። ያሁሉ ወጣት በጥቂት እራሳቸውን በማያውቁና ሕይወታቸው ሠባራ በሆነ ግለሰቦች ሲታመስ፣ ሲንገረገብና ሲቆላ ያሳያል። የወጣቱ የመከራ የስቃይ ጩኸት ይሠማል። የተተለተለው ገላቸው ይታያል። የበሰበሰው ቁስላቸው ሽታ ይሸታል። የወጣቱን የመከራ ውስጥ ሕይወት አገላብጦ ያሳያል። እስከ ዛሬ ስለኢሕአፓ ከተነበቡት መጻህፍት ውስጥ በታሪክ ማስረጃነት ከቀረቡት መካከል የያ ትውልድ "***ፍጹም ነው እምነቴ***" ለየት ይላል። ብዙዎቹ ሌሎች መጻህፍት፣ የኢሕአፓን ታሪክ፣ አጀማመር፣ የትግል ጉዞና ሂደት፣ አንድነትና ልዩነትን፣ ዉጣ ውረድና ቅንብርን አስጨብጠውናል። "***ፍጹም ነው እምነቴ***"ም በተመሳሳይ ሁኔታ የቀረበ ቢሆንም ከሌሎቹ የሚለየው የኢሕአፓን ወጣት ክንፍ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ (ኢሕአወሊ)" የተጋድሎ ስራዎችና እያንዳንድዋን የከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር ሂደት፣ ሽባሪዎችን፣ የማሰቃያ ዘዴአቸውን፣ ጭካኔአቸውን እንዲሁም የወጣቱን ፍጹማዊ አስተዋጽዎ፣ ቆራጥነት፣ አልበገሬነትና የሞተው ሞቶ የተረፈው እንደገና መደበኛ ኑሮ ውስጥ ገብቶ የነበረውን የቁጭት ጉዞ ያሳያል። አንዳንዶቹም ዘር እስከ መጨረሻው አያዩም፣ አንዳንዶቹም አእምሮዋቸው እስከ ዘለዓለሙ መሸኩዋል፣ የአፍላ ዕድሜያቸውን ሳይሞቁት አመድ ሆነዋል። ይህንን ብሶት ሁሉ ከፍለው አሁንም "ፍጹም ነው እምነቴ ኢትዮጵያዊነት ነው ሞቴ" እያሉ እንደገና የማይበግር ክንዳቸውን ያነሳሉ። ይህ ባይሆን ኖሮ "***ፍጹም ነው እምነቴ***"ና ሌሎቹም የነ ቆንጂትን "***ምርኮኛ***" የአስማማውን "***ኢሕአሠ***" ዓይነት መጽሀፎች አይታዩም ነበር። የኢትዮጵያ አምላክ በነሱ ላይ ይደር፣ ሀይሉን ይስጣቸው!!!

የ "***ፍጹም ነው እምነቴ***" ዘገባ በሚነበብበት ጊዜ የተለያዩ ሀሳቦች በህሊና ውስጥ እንዲተራመሱ ያደርጋል። እንዴት ይህ ሕገ ወጥ ግፍ በኢትዮጵያ ቦታ ሊሰጠው ቻለ? እንዴት ተዉ ባይ ጠፋ? ያ ሁሉ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት አዛዥና ባለስልጣን ለሀገሩና ለሕዝቡ በህግ ፊት በመሃላ የገባውን ቃል-ኪዳን ከዶ፣ በአንድ ወስላታ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ሥር ወደቀ? የተማሩ ናቸው የተባሉትስ የመኢሶን ሰዎች ከደም መፋሰስ ይልቅ እንዴት ሌላ አማራጭ መንገድ አጡ? የተማሩ የተባሉትስ የኢሕአፓ መሪዎች በወቅቱ ማፈግፈግ እንዴት አልቻሉም? የሚሉት ጥያቄዎች ይቆጠቁጣሉ። ያጣነው ትውልድ እኮ እልቆ መሳፍርት የለውም። ለካ የውሸት ሕግ፣ የውሸት ሠራዊት፣ የውሸት ፖሊስ፣ የውሸት ምሁር ነበር የነበረን! ነው ያሰኘኝ። በማናቸዉም ዓለም፤ በማናቸውም ታሪክ፣ ወታደር አብዮተኛ ሆኖ አያውቅም፣ አገር አበልጽጎ፣ ፍትህ አንግሶ፣ ዲሞክራሲ አንጥፎ፤ የሰላም አባወራ ሆኖ አያውቅም። ወታደር ሰላምን እንኩዋ የሚያዉቀው ሲሸነፍ ነው፤ ከዛ ውጪም ሰላምና ዲሞክራሲ ካሰረጸ ወታደራዊ አይደለም። ወጣቱ ለካ ይህንን ተገንዝቦ ነበር፣ የሞት የሽረት ትግል ውስጥ የገባው!

የዛን ግዜው ወጣት ትውልድ በእውነቱ ለኢትዮጵያ ገጸ በረከት ነበር፣ አሁንም ነው። እነዚያ ታናናሽ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በዛ በለጋ ዕድሜአቸው የሀገርና የሕዝብ ጠበቃና ዘብ ሆነው የከፈሉት መስዋዕትነት ኢትዮጵያዊነትን ያንፀባርቃል። ከባርነት ነፃ አውጥተውን በክብር እንድንኖር ያደረጉንን አባቶቻችንና እናቶቻችንን በአካልና በአምሳል፣ እነዛ ታናናሽ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ተክተዋቸዋል። አሁንም ተስፋችን በእነሱ ነው።

በእኛ ዕድሜ በባለ ሰባዎቹ፣ ወላጆቻችን ነፃነታቸውንና ስብዕናቸውን ለመግፈፍ የመጣዉን የወራሪውን የጣልያን ጦርና ተከትሎዋቸው የመጣውን ቅጥረኛና አድርባይ የባንዳ ሠራዊት ለመቁዋቁዋም የተደረገውን ተጋድሎ ሲተርኩልን በሀዘን ስናደምጥ፣ ጥይት የበሳውን ገላቸውን፣ ቦንብ የነደለው አጥንታቸውን እያየን ስናዝን፣ ከዛ በሁዋላም ድል ከተቀዳጁና

ጠላታቸው በእጃቸው ከወደቀ በሁዋላ፣ ጣልያኑንም ባንዳውንም እየገረፉና እያዋረዱ የፊጥኝ አስረው ያደረጉትንና የተሰማቸውን ኩራትና ክብር ሲተርኩልን እየተደሰትን እንደፊልም ደጋግመን እየሰማን በህሳብ እያየን አደግን።

የአቶ ነሲቡም መጽሐፍ፣ ልክ እንደአባቶቻችን ትረካ፣ የሕይወት፣ የትግል፣ የውጊያ፣ የመከራ ታሪክን እንደፊልም ብቻ ሳይሆን፤ የመከራውን ጩኸት፣ የቁሱሉን ሽታ፣ የሞትን ጣር ያሳያል። በእብሪተኛነት ሆዱ ላይ በጥይት የመታውን ከፈለኝን ፣ የሚያጣጥረውና በደም የተዘፈቀው የቀበሌ 33ቱ ብችሩ፤ ገዳዩን ከፈለኝን "ጋሽ ከፈለኝ ሆስፒታል ብትወስደኝ እኮ እድናለሁ" ብሎ የተማፀነውን የንፁህ ወጣት ቃለ-ሲቃ ሁኔታ ሳነብና እብሪተኛው ከፈለኝ ሲለመን "ተውት ሆዱ ዉስጥ ጥይት ይሸከም" ብሎ የመለሰዉን ሳዳምጥ፣ ድርጊቱ እውነት ከፊቴ የተደረገ መስሎኝ አእምሮዬ ደፈረሰ፣ ሰውነቴ ተቆጣ፣ ትኩስ የመንፈስ ቁስል አብሰለሰለኝ፣ ደም ግፊት ወጋኝ። መጽሀፉን ከደንኩት።

አባቶቻችንና እናቶቻችንስ መከራቸውን ለአምስት ዓመት ቢያዩም ድልን ቀምሰዋል፣ ተጐናጽፈዋል። ክብርና ኩራትን፣ ደስታንና ነፃነትን ጨብጠዋል። ያ ትውልድ ግን ድልን ሳያይ እንደመሸበትና እንደጨለመበት በህይወቱ ላይ ጠባሳና ቁስል ተሸክሞ ይዞራል፣ ይኖራል። ይህ የአቶ ነሲቡ መጽሐፍ ደግሞ ለዛ ትውልድ ቁስሉንና ጠባሳውን እንዲያረግፍ የጥሪ መጽሀፍ ነው። "የዓላማችን መሸነፍ መሸባት እንጂ ድል አልመሸባትም" ነው የሚለው። "ፍጹም ነው እምነቴ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ" ብሎ የተነሳው ቆፍጣናው ወጣት በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን ይቆጠራል፣ ተምሩዋል፣ በስሉዋል፣ በቂ ተመክሮ አለው፣ እራሱን መምራት ይችላል፣ በጐልማሳ ዕድሜ ውስጥ ይገኛል፣ ሌላ መሪ አያስፈልገውም። የቀድሞ የኢሕአፓ መሪዎችማ ለ40 ዓመታት "ጎሽ" የማይባሉ መሆናቸውን በራሳቸው ላይ መስክረው፣ አሁንም በቀድሞ ታዋቂ ስራዎችና ታዋቂ ታጋዮች ምስለ-ጥላ ሥር ራሳቸውን ያንፀባርቃሉ። በያሉበት እያደጉ ሳይሆን እየመነመኑ፣ እየጠነከሩ ሳይሆን እየደነበሹ ይታያሉ። ዳገቱን ሳይሆን ቁልቁለቱን እንኳ መውረድ ተስኑዋቸው በእጃቸው የነበረውን ወጣትና ደጋፊ ማሰባሰብ እንኳ አልቻሉም። ኖር የሚላቸው ቀርቶ ከበር የሚላቸው የለም። ይህ መጽሀፍ እኰ ይናገራል፣ ይጣራል። ግን የቀድሞ መሪዎችን ከበር አላለም።

ያ! ጠላተ ብዙ የነበረ ኢትዮጵያዊ ኢሕአፓ ምስጢሩ አልዘልቆት ኖሮ በስድስት መአዘን ተወቀጠ። ዉስጡም በአረምና ዋግ ተመታ፣ በአልቅቶችም ተተበተበ፣ ዉስጠኛ ሰላቢዎች ለሳኑንም ክንዱንም አዛሉት፣ እሳተ መለኮቱንም አመከኑት። ያም ቢሆን አንዳንድ የቀድሞ መሪዎች ዳገትም አይውጡ ቁልቁለትም አይውረዱ፣ ግን የገቡበትን የትግል አርማ ይዘው በቃል ኪዳን ለኢትዮጵያ ህዝብ ከሰጡት የተስፋ ቃል ስር እስከ አሁን መገኘታቸው ለዘመናት ሊያስከብራቸው ይገባል። በተቃራኒ ግን እና ደግሞ ለኢትዮጵያ ወላጆች የገቡትን ቃል ኪዳን ክደው፤ ጉዋደኞቻቸውን ክደው፤ መሀበረሰብንና ድርጅታቸውን ክደው፣ ለገንዘብ ተሽጠው ተለውጠው፣ ህዝባቸውን ሽጠው፤ የድሜልክ የወላጅ ቅርሰ-ቅስም ሰባሪ ሆነው፣ ላገር ሰው እሮሮ ተክለው፣ በግድ የለሽነት ያጠፉትን አጥፍተው፡ አገርና ሕዝብ ክደው ጠፍተው ተሰውረው የሚኖሩትን አንዳንድ የቀድሞ አልባሌ መሪዎች፣ "***ፍጹም ነው እምነቴ***"ን አገላብጦ አዟዊዞሮ ከልሶና አቂያቂሮ ለሚያነብ አበሻ፣ ትዝብቱን ቁልጭ አድርጎ ይስጨብጣል።

"***ፍጹም ነው እምነቴ***" መጽሀፍ በመኢሶን ውስጥ የነበሩ ወጣቶችን እንኩዋ ግምት ይሰጣል። ለተወሰዱ የተሳሳቱ እርምጃዎችና ማግለሎች ፀጸቱን ያሰማል። መብሰል መንተክተክ አገራዊነት አይደለምን!? ይህ መጽሀፍ ስለከፍተኛ 15 ተጽፎና፣ ስለሌሎቹ 24 ከፍተኞች ባይናገርም፣ የቀሩት ከፍተኛ ወጣቶችን ታሪካችሁን ፃፉ ይላል። ከከፍተኛ 15 አኳያ ከፍተኛ 9፣ 10፣ 12 እና ሌሎቹም ውስጥ በእነ ቀልቤሳ፣ በእነ እንዳለ፣ በእነ ኪዳኔ፣ በእነ ሰለሞን የተሰሩት ግፎች ከከፍተኛ 15 አይተናነሱም። በቸሃ፣ በሆሳህና፣ በደብረ ማርቆስ፣ በጐንደር፣ በወሊሶ፣ በአዋሳ፣ በሐረር ወዘተ የተሠሩት ግፎች ወደር የላቸውም። "***ፍፁም ነው እምነቴ***" የዛን የመከራ ቀን ተሸክመው ለሚኖሩ ወጣቶች ታሪካቸውን እንዲመዘግቡ ጥሪ ከማድረጉም በላይ ያ ትውልድ www.yatewlid.org, www.yatewlid.com የሚል ድረ ገጽ መዘጋጀቱንና ሁሉም ወጣቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

ያንን አሰቃቂ የቀይ ሽብር የሀገርና የህዝብ ማጥፋት ወንጀል ከፈጸሙት በግምት ቆጠራ 6800 ሰዎች ውስጥ ከ3000 በላይ ለፍርድ አልቀረቡም። የአገሪቱ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስራዓት የአስቃቂ ወንጀሎች ክስ አመሰራረት ህግንና ደንብን ያልተከተለውና ሳይጀመር የተሰናከለዉ የወያኔ-ኢሕአዴግ ፍርድ መድረክ እንኩዋ፣ ተከሠው ወንጀለኛነታቸው ከተረጋገጠባቸው 3583 የቀይ ሽብር አራማጆች ውስጥ 1308 የሚሆኑት አልተገኙም። እነዚህ ወንጀለኞች የት ይኑሩ የት ለወያኔ-ኢሕአዴግ ጉዳዩ አይደለም። በህይወት ያሉ የዚያ ጊዜ ወጣቶች ግን ከፈለኝንና ቀልቤሳን ከመሸጉበት የውጭ ሀገር

ጓዳ ፈንቅለው እንዳወጧቸው ሁሉ ሌሎቹን የማውጣት ግዴታ የአገር ልጅ ሁሉ ግዴታ መሆኑን “***ፍፁም ነው እምነቴ***” ያስገነዝባል።

እነዚህ ሕወሀት/ኢሕአዴግ ተሠወሩ ያልዋቸው 1308 ወንጀለኞች ማንነት፣ አድራሻ፣ ግንኙነት፣ ፎቶ ግራፍ ለሕዝብ አልቀረበም። ለዓለም አቀፍ የወንጀል ክትትልም (ኢንተርፖል) ወያኔ-ኢሕአዴግ የተፈላጊንት መረጃ አላቀረበም። የሰው ዘር የጨረሰው መንግስቱ ኃይለማርያምም ለዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አልቀረበም። ለኢትዮጵያ ህዝብም እነዚህን የተሰወሩ ወንጀለኞች አድኖ የመያዝ መብት አልሰጠም። እነዚህን ወንጀለኞች የሚፈልግና የሚያድን ተቋዋም ሆነ መመሪያ አላየንም። እሺ አንዳንዶቹ የሕወሀት አንዳንዶቹ የሻቢያ አባላት በመሆናቸው ይደብቁዋቸው። ሌሎቹ ግን እንዳይታወቁ የሚከለከልበትና የሚደበቅበት ምክንያት ምንድን ነው? ሕወሀትም ቀይ ሽብርተኞችም አንድ በመሆናቸው ይመስላል።

የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሰቆቃ አራማጅ ግለሰቦች ሲታደኑ ይሄው  ወደ ሰባ ዓመት ሊደርስ ነው። የኛዎቹም ረሻኞች ሲታደኑ መኖርና ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል። በአዲስ አበባ ያለውም የሰማዕታት መታሠቢያ ሙዚየም ተቁዋም የያ ትውልድን ታሪክና መረጃ ከመጠበቁ ጋር ይህን አሰቃቂ ምግባር የፈጸሙትን ወንጀለኞችን ለፍርድ ማቅረብ ተግባር መረከብ ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ፣ ስራውን የሚያሰራው ፈቃጅ መንግስት ከተገኘ።

የዓላማ መሸነፍ ይመሸበታል እንጂ ድል አይመሽባትም። በግፍ ያለቁት የታናናሽ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደም አሁንም ይህንኑ ይጮሃል። የሀገራችን ህዝብ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ግፍና ውድቀት ደርሶበታል። ይህ የቆሰለው ህብረተሰባችን ለታላቁ ሤራ ተጋልጡዋል። ቁስሉ ሳይድን ቢቀርም “***ፍጹም ነው እምነቴ***” “ኢትዮጵያዊነት ነው ሞቴ” የሚሉ መጽሃፍትን መልዕክት በማገናዘብ ወደ ኢትዮጵያዊነቱ እንዲያንሠራራ ይረዱታል ብዬ አምናለሁ።

አመሰግናለሁ

solomonKB@yahoo.com

ኅዳር፣ 2007 ዓ.ም.